
የሚሰማ ጆሮ
ያለው ይስማ!
የመምህርነት ሙያ እና
የትምህርት ጥራት በኢትዮጵያ
ከሙያ-አልባ መምህር ወደ
መምህር-አልባ ክፍል ወይስ?
አክሊሉ ዳለሎ (ፕሮፌሰር)
"ይህ መጽሐፍ... ለመምህርነት ሙያ የፖሊሲ ግብዓት በመሆን፣ መሠረታዊና ዘለቄታ ያለው ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችልና፣ ለአገራችንም ብሩህ ተስፋ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ።"
ሎሬት ፕሮፌሰር ጥሩሰው ተፈራ
፳፻፲፯
ዓ.ም

**የመጽሐፉ የፊት ገፅ ማብራሪያ (በብሩክ ጌታሁን)፡**

- የመማሪያ ክፍሎቻችን ብርሀን እየጨላለመ እንዳለ ያመለክታል፣
- የክፍሉ ግድግዳ በቆየ ቴክኖሎጂ፣ መጠናቸው በማይመሳሰል፣ ዝብርቅርቅ ድንጋዮች የተዋቀረ ነው፤ ይህም አሁን ያለውን የአገራችን የትምህርት ሁኔታ ይገልጻል፣
- የትምህርት አሰጣጥ መንገዳችንና መርጃ መሳሪያዎቻችን በሰሌዳው ሊገለፅ እንደተሞከረው ወደ መውደቅ ያዘመሙ ይመስላል፣
- ስለዚህም ትኩረታችንን (በመብራቱ መጉላት ለማሳየት እንደተሞከረው) ወደ መምህርነት ሙያ እና የትምህርት ጥራት ላይ እናድርግ፣ እና
- የአስተማሪው ምስል ውስጥ አለመኖር "መምህር-አልባ ክፍል ወይስ...?" ለሚለው ከንካኝ ጥያቄ ክብደት ይጨምርበታል ተብሎ ይታሰባል።

# የመምህርነት ሙያ እና የትምህርት ጥራት በኢትዮጵያ

## ከሙያ-አልባ መምህር ወደ

## መምህር-አልባ ክፍል ወይስ?

**አክሊሉ ዳለሎ (ፕሮፌሰር)**

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣
የትምህርትና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ፣ የመምህራን ትምህርት ክፍል

አዲስ አበባ
ሐምሌ 2017 ዓ/ም

**© አክሊሉ ዳለሎ (ፕሮፌሰር)**
**የመጀመሪያ እትም፣** ሐምሌ 2017 ዓ/ም

የጸሐፊው መብት የተጠበቀ ነው።

ያለጸሐፊው ፈቃድ ይህን መጽሐፍ ማባዛት፣ መቅዳት፣ ማሳተምና በማንኛውም ሌላ መንገድ ማሰራጨት የተከለከለ ነው። ሆኖም ተገቢውን ሥነጽሑፋዊ የምንጭ አጠቃቀስ ሥርዓት በመከተል ለጥናት እና ለማስተማሪያነት መጠቀም ይቻላል።

**© Aklilu Dalelo (Professor)**
**1st Edition,** July, 2025

All rights reserved, including the right to reproduce the book or portions thereof in any form whatsoever.

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመጻሕፍት እና ቤተመዛግብት ኤጀንሲ የተመዘገበ
ISBN: 978-99990-0-803-7

**የሽፋን ድዛይን፡** ብሩክ ጌታሁን (+251913638898)
**የውስጥ ድዛይን፡** ብሩክ ጌታሁን (+251913638898) እና
ክራንስ አክሊሉ ዳለሎ (+251923274198)

**መጽሐፉ እንደሚከተለው ሊጠቀስ ይችላል፡**
አክሊሉ ዳለሎ (2017 ዓ/ም). የመምህርነት ሙያና የትምህርት ጥራት በኢትዮጵያ፡ ከሙያ-አልባ መምህር ወደ መምህር-አልባ ክፍል ወይስ? አዲስ አበባ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ

**Citation:**
Aklilu Dalelo (2025). The Teaching Profession and Quality Education in Ethiopia: From Teachers with No Competence to Classes with No Teachers OR? Addis Ababa: Addis Ababa University Press

**አስተያየትዎን በሚከተለው አድራሻ ያድርሱን፡**
***አክሊሉ ዳለሎ (ፕሮፌሰር)***
***ፖ.ሣ.ቁ.*** ***150203፣ አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ***
***ስልክ፡*** +251 965468660

***ኢሜይል፡*** aklilu.dalelo@aau.edu.et
akliludw@gmail.com

## የቀዳሚ አንባቢያን አስተያየት

ይህ በፕሮፌሰር አክሊሉ ዳለሎ የቀረበልን መጽሐፍ በመምህርነት ሙያና የትምህርት ጥራት መካከል ያለውን ቁርኝት በብዙ መረጃ በመተንተን ጥራት ያለው መምህር በሌለበት ጥራት ያለው ትምህርት መፈለግ “ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ” ከመሆን አይዘልም በማለት ይሞግታል። ፕሮፌሰር አክሊሉ የዳሰሳ ጥናትና በመስኩ ምርምር በማካሄድ የመምህርነት ሙያ በአገራችን የደረሰበትን ደረጃና ክብር በመተንተን ቁልጭ አድርጐ በቀላል ቋንቋ ለአንባቢ አስቀምጧል። እንደሚታወቀው ሁሉ በኢትዮጵያ ትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታ ላይ የቀረቡት ምክረ-ሃሳቦች በተከታታይ በወጡት የሀገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፓሊሲና ሕግ ላይ ያደረጉት ተፅዕኖ ቀላል አይደለም። ይህ እውነታ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በስፋትና በጥልቀት መዳሰሱ የመጽሐፉን ጠቀሜታ ዘመን ተሻጋሪ ያደርገዋል። ጸሐፊው በመምህርነት ሙያ ዙሪያ የሚስተዋለው አሳሳቢ ሁኔታ በአስቸኳይ መፍትሔ ተፈልጐ ካልተስተካከለ የትምህርት ጥራትም ሆነ አገሪቷ ልትደርስበት ካለመችው የልማትና ብልፅግና ማማ መድረስ እንደማትችል በማያሻማ መልክ አቅርቧል። ዘርፉ ጥገናዊ ሳይሆን ሥር-ነቀል የፖሊሲና የአመለካከት ለውጥ እንደሚያስፈልገው ተመላክቷል። የመምህርነት ሙያ እንዴትና በምን መልክ በአገራችን መሻሻልና መደራጀት አለበት ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄም ጸሐፊው መፍትሔውን ከመተንተንና ከመጠቆም ወደ ኋላ አላለም። የፕሮፌሰር አክሊሉ መጽሐፍ ከተጠቀምንበት ለመምህርነት ሙያ የፖሊሲ ግብዓት በመሆን መሠረታዊና ዘለቄታ ያለው ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችልና ለአገራችንም ብሩህ ተስፋ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ።

***ሎሬት ፕሮፌሰር ጥሩሰው ተፈራ***
የትምህርትና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ይህ በፕሮፌሰር አክሊሉ ዳለሎ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀው መጽሐፍ በኢትዮጵያ የመምህራን ሥልጠና ልማት ዘርፍ ከዘመናዊ የትምህርት መጀመሪያ አንስቶ በሳይንሳዊ መንገድና አሳማኝ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የተጻፈ ሲሆን በአጠቃላይ ከዚህ በፊት በተበታተነ ሁኔታ በወጉ ያልተሰነዱ፤ የታተሙም ሆነ ያልታተሙ ጥናታዊ ጽሑፎችንና የፖሊሲ ሰነዶችን በማካተትና በመተንተን በግሩም ሁኔታ የቀረበ ነው። በመሆኑም በትምህርትና በአጠቃላይ አገራዊ ልማት ላይ አትኩረው ለሚመራመሩ ምሁራን፤ በቅደመ-ምረቃና በድህረ-ምረቃ ደረጃ ላሉ ተመራማሪዎች እንዲሁም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ እጅግ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው፡፡ … ወዳጄ ፕሮፌሰር አክሊሉ እንኳን ደስ ያለህ እያልኩ መጽሐፉ ሲታተም የመጀመሪያ ገዢ እኔ መሆኔን አረጋግጥልሃለሁ፡፡

***ተሰፋዬ ሰመላ (ፕሮፌሰር)***
የትምህርት ኮሌጅ፣ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

ትምህርት የምንለው ጉዳይ በጥቅሉ በወል ተስማምተን፣ ልምዳችንን ቀምረንና ሥርዓትን አበጅተን ዜጋን የምናሳድግበት ተግባር ነው፡፡ የዚህ ተግባር ዋናው የሥራ መሪ ደግሞ መምህሩ ነው፡፡ ምንም እንኳ የትምህርት ጥራት ሁሉም ነገሩ በመምህሩ ላይ የተንጠለጠለ ነው ባይባልም የመምህሩ ሚና ግን ከሌሎች የትምህርት ግብዓቶች በሙሉ የላቀ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ከታሪክም አንፃር ሲታይ የማንም አገር ትምህርት ጥራት ከመምህሩ ልቆ የታየበት ጊዜ የለም፡፡ አንድ ፈላስፋ፣ ዜጋህን አሳየኝ መምህሩ ማን እንደሆነ እነግርሃለሁ እንዳለው መሆኑ ነው፡፡ ይህ ሙያ በኢትዮጵያ ዘለግ ያለ ዕድሜ ቢያስቆጥርም በዕድሜው ልክ ግን አልተነገረለትም፤ አልተዘከረለትም፤ አልተጻፈለትምም፡፡ ያውም፣ ደግሞ በዚህ በፕሮፌሰር አክሊሉ ዳለሎ መጽሐፍም በደንብ እንደተተነተነው፣ ሙያው ይልቁንም በበርካታ ተቃርኖዎች ተሞልቶ እየታየ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌም ያክል:- ክብርና ዋጋ ከራሳችንም ቢሆን አስበልጠን የምንሰጣቸውን ልጆቻችንን በቂ ክብርና ዋጋ የማንሰጠው መምህር እንዲያሳድግልን ማድረጋችን፤ የበለፀገ አገርን በደከመና በተጎዳ መምህር የመገንባት ያልተጻፈ እሳቤ፤ አገሪቱ በሰው ኃይል ራሷን እንድትችል መምህር ያደረገውን በጎ አስተዋጽዖ ችላ እያሉ የዛሬ መምህር ብቃት የጎደለውና ሥነምግባር የሌለው እንደሆነ በየአደባባዩ በጅምላ መተቸትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህ አኳያ የመምህርነት ሙያ አሁናዊና ታሪካዊ ዳራ በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል ፕሮፌሰር አክሊሉ ዳለሎ በሚገርም ጥልቅ ትንተናና በተለይም በአማርኛ ቋንቋ ጽፎት ሳገኝ በጣም ተደሰትኩኝ፡፡ መጽሐፉ በዘርፉ በሚገኘው በርካታ እውቀትና በማውቀው በፕሮፌሰር አክሊሉ የዳበረ የማስተማር፣ የምርምርና የማህበረሰብ ልምድ

የታጨቀ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ትኩረት ለተነፈገው ሙያ ትኩረትን፣ ለአንባቢያን በሥነትምህርት ሳይንስ ጠብሰቅ ያለ እውቀትን፤ በዘርፉ ላሉ ምሁራን ከተምሳሌነት በተጨማሪ የማጣቀሻ ጽሑፍ አገልግሎትንና ለማህበረሰቡና ለመንግሥት ደግሞ አገርን ለመታደግ የማንቂያ ደወል የመሆን አገልግሎት እንዲሰጥ ስለመዘጋጀቱ ረቂቁን ሳነብ በደንብ ተረድቻለሁ፡፡

***በላይ ተፈራ (ፕሮፌሰር)***
የሳይኮሎጂ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

*መጽሐፉን ለተከታታይ ቀናት በተመስጦና በአድናቆት አንብቤአለሁ። ራሴን ከአንደኛ፣ ሁለተኛና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስገብቼ እንደ ተማሪም እንደ መምህርም እየሆንኩ ከመጽሐፉ ብዙ ተምሬአለሁ። ይህ መጽሐፍ ከአፀደ ህፃናት እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ላለው ተማሪና መምህር ምርጥና ድንቅ ትምህርት ቤት ሆኖ አግኝቻለሁ። የመጽሐፉ ደራሲ የመምህርነት ሙያና የትምህርት ጥራት ተኮር በርካታ አገራዊና ውጫዊ ጥልቅና ሰፊ የሳይንሳዊ ጥናት፣ ምርምርና ዳሰሳ ውጤቶችን በዋቢነት አካቷል። የሌሎች አገራትን ተሞክሮና ልምድ ለሁሉም አንባቢ ህሊና በንፅፅር አስቀምጧል። በአገራችን መፍትሔ ያላገኙ እውነታዎችን፣ ውሳኔዎችንና አዋጆችን በቁጭት ይፋ አድርጓል። ለመምህርነት ሙያ ክብር፣ ለመምህራን ብቃትና ክህሎት፣ እና ለትምህርት ጥራትና ለሀገር እድገት ችግሮች ዝርዝር የመፍትሔ ምክረ-ሃሳቦችን አቅርቧል። ሁሉም ያድምጥ!*

***ፕሮፌሰር ተሰማ ኤርሱም***
ቀዶ ህክምና ትምህርት ክፍል፣ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በቅድሚያ ጸሐፊው ይህንን ትልቅ ዘመን ተሻጋሪና ለአገርም ለትውልድም ጠቃሚ የሆነ ሥራ ሠርተው ለአንባቢ በማበርከታቸው ሊመሰገኑ ይገባል፡፡ ይህንን ምናልባትም በአገራችን በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን አበርክቶ ልዩ የሚያደርገው ጸሐፊው የተጠቀሙባቸው የማጣቀሻ ምንጮች እጅግ ተዛማጅ፤ ወቅታዊና፤ በርከት ያሉ በጥናትና ምርምር ላይ የተመረኮዙ መሆናቸው ነው፡፡ ይህም ጸሐፊው ለጉዳዩ የሰጡት ከፍተኛ ትኩረትና ጥንቃቄ፤ የከፈሉት የጊዜ፣ የገንዘብና፣ የእውቀት ዋጋን የጎላ ያደርገዋል። በተጨማሪም መጽሐፉ ጸሐፊው ለሙያው ያላቸውን ፍቅርና ቁጭት በግልጽ ያሳያል፡፡ ይሄ ደግሞ በአንፃሩ የጽሑፉን ተአማኒነትና ግዝፈት እና ልህቀት ያመላክታል፡፡ ይህ መጽሐፍ ከፍተኛ ልብ አንጠልጣይ ግርምትን የሚጭሩ፤ የሚያስደንቁ በአንፃሩ ደግሞ እጅግ የሚያሳዝኑ፤ የሚያስደምሙ የመምህርነትና መምህራን አገርአቀፍና ዓለምአቀፍ ጉዳዮችን የሚዳስስ ነው። ምናልባትም እኔ በሙያው ውስጥ ስላለሁ ነው መሰለኝ በታሪኩ በጣም ልቤ ተነክቷል፡ ፡ የታሪኩ አወቃቀርና አቀራረብም ለጽሑፉ ሥጋ አላብሶ ነፍስ ዘርቶበታል፡፡ አንዱ ታሪክ ከሌላው ጋር ያለው ቁርኝት በግልጽ እስከመጨረሻው ድረስ ስለሚታይ አንባቢ ታሪኩን ለመረዳት አይቸገርም፡፡ ሌላው ጸሐፊው የተጠቀሙበት ቋንቋ ቀላልና ሁሉም አንባቢያን ዘና ብለው እንዲያነቡ ይጋብዛል፡፡ ሥራው በአማርኛ ቋንቋ በመቅረቡ ደግሞ ተደራሽነቱ ከፍ ያለ ነው፡ ወደፊት በሌሎችም አገርኛና ዓለምአቀፍ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ቢቀርብ የመረጃ ጠቀሜታውና ተደራሽነቱ ይበልጥ ከፍ ሊል ይችላል፡፡ በመጨረሻም ሁሉም ባለድርሻ አካላት የመምህርነት ሙያ ከፍተኛ አደጋ ላይ መሆኑን ተገንዝበው ዛሬ ነገ ሳይሉ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ መጽሐፉ በአፅንዖት ይመክራል፡፡

***ሐረገወይን ፋንታሁን (ፒ. ኤች.ዲ)***
የትምህርትና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የመምህርነት ሙያ እድገት በኢትዮጵያ ከየት ወደ የት እንደሄደ ጠቃሚ መልዕክት በፕሮፌሰር አክሊሉ ዳለሎ በጥልቅ ገለፃ፣ የመምህርነት ታሪካዊ ደረጃዎች፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለምን እንደወረደም ጭምር ተገቢና ሳይንሳዊ ምክንያቶችን በመጠቆም፣ እንዲሁም የመምህርነት ሙያ ታሪካዊ ሂደትን ከክፍል ክፍል፣ ከዩኒት ዩኒት፣ እንዲሁም ከንኡስ ርዕስ ንኡስ ርዕስ የሥነ-ትምህርት የይዘቶች ቅንብር መርህን ተከትሎ ተጽፏል፡፡ በመሆኑም የመጽሐፉን የተለያዩ ክፍሎች ሳነብ የማንበብ ፍላጎቴ ከምዕራፍ ወደ ምዕራፍ ስሸጋገር በከፍተኛ እየጨመረ እንዲሄድ ማድረግ ችሏል፡፡ ለረዥም ዓመታት በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ እንደሰራ ሰው የመምህርነት ሙያ በኢትዮጵያ ከየት ወደ የት የሚለውን ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖረኝም ይኸን ፍላጎቴን ሊያረካ የሚችል መጽሐፍ በማጣቴ ምክንያት ለረዥም አመታት ፍላጎቴን ገታ አድርጌ ብቆይም፤ ይኸው በፕሮፌሰር አክሊሉ ዳለሎ መጽሐፍ ምክንያት የማወቅ ፍላጎቴ

መርካት ችሏል፡፡ ስለሆነም ሁላችሁም ይኸን መጽሐፍ በማንበባችሁ የመምህርነት ሙያ በኢትዮጵያ ከየት ወደ የት ለሚለው ጥያቄያችሁ ትክክለኛ ምላሽ ልታገኙ እንደምትችሉ ከፍተኛ ግምት አለኝ። መልካም ንባብ ለአንባቢያን፤ ዕድሜና ጤና ለጸሐፊው ፕሮፌሰር አክሊሉ ዳለሎ።

***ሰሎሞን መለሰ (ፕሮፌሰር)***
የትምህርት ኮሌጅ፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

የ"የመምህርነት ሙያና የትምህርት ጥራት በኢትዮጵያ"ን መጽሐፍ ረቂቅ አንብቤዋለሁ። መጽሐፉ የአገራችንን የትምህርት ጥራት ችግሮችን በሰፊው በመዳሰስ ወሳኝ በሆኑ የጥራት መጓደል መንስኤዎች ላይ ሰፋ ያለ ትንተና ይሰጣል። የመምህራን አቅርቦትና ጥራትን በተመለከተም እንደአንድ የትምህርት ሥርዓቱ መሠረታዊ ችግር ሰፊ ዳሰሳ አድርጓል። በአቀራረቡ ወትሮውን እንደሚታየው እንደወረደ (sheer description) ሳይሆን በተወሰነ ደረጃ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይሞግታል። ምንም እንኳን ጸሐፊው የቀደሙ አገርኛ "ጥናታዊ ጽሑፎች"ን ወይም ማጣቀሻዎችን በመጠቀም ካቀረቧቸው አስረጂዎች ጥቂቶቹን በተመለከተ መጠነኛ ልዩነት ቢኖረኝም፤ መጽሐፉ በዚህን ወቅት መጻፉን እጅግ በጣም ወድጄዋለሁ። የትምህርት ባለሙያዎች፤ በታሪክ አጋጣሚ ያለበቂ ልምድና የትምህርት ዝግጅት በየደረጃው የትምህርት ሥርዓቱን እየመሩ ያሉ፣ እንዲሁም የተማሪ ወላጆች ይሄንን መጽሐፍ ቢያነቡ እንደሚጠቀሙ ላስገነዝብ እወዳለሁ። በከፍተኛ ትምህርት የሥነ-ትምህርት መምህራንና ተመራማሪዎች እንዲሁም በትምህርት ሥርዓቱ ስለሚታየው ውድቀትና ውዥንብር መንፈሳዊ ህመም የሚሰማቸው ሁሉ መጽሐፉን እንዲያነቡ እመክራለሁ።

***አምበሳ ቀነአ ቦሩ (ፕሮፌሰር)***
የትምህርትና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በፕሮፌሰር አክሊሉ ዳለሎ የተዘጋጀውን "የመምህርነት ሙያና የትምህርት ጥራት በኢትዮጵያ: ከሙያ-አልባ መምህር ወደ መምህር-አልባ ክፍል ወይስ?" የተሰኘውን መጽሐፍ በጥልቀት አንብቤዋለሁ፡፡ መጽሐፉ በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ ጠለቅ ያለ ትንተና የተካተተበትና ሥርነቀል በሚያስብል ዓይነት የአፃፃፍ ስልት የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያን የመምህራን ሙያና የመምህራን አሠላጣጠን በተለየ አቀራረብና በድፍረት ፍንትው አድርጎ በአገራዊ ቋንቋ በማቅረቡ በአይነቱ የተለየ ምናልባትም የመጀመሪያው ሊያደርገው ይችላል፡ ፡ ፕሮፌሰር አክሊሉ በኢትዮጵያ በመምህርነት ሙያ እና በመምህራን ላይ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በመንግሥትና በህብረተሰቡ ዘንድ ተነፍጎት የነበረውንና አሁንም ያለውን የትኩረት ማጣት፣ ተገቢውን ሙያዊ ክብር መንፈግና ይህም ያስከተለውን የትምህርት ጥራት መዘዝ አስረጂዎችን በመጥቀስ በድፍረት "ጆሮ ያለው ሁሉ ይስማ" በማለት ሞግተዋል። ፕሮፌሰር አክሊሉ የኢትዮጵያን የትምህርትና የመምህራን ችግሮች በማብራራትና በመተንተን ብቻ አላቆሙም፡፡ ሊተገበሩ የሚችሉና ቢተገበሩም መሠረታዊ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ምክረ-ሃሳቦችንም አቅርበዋል፡፡ ይህ መጽሐፍ በተለይ ለኢትዮጵያዊያን መምህራን አሠልጣኞች (አዘጋጆች)፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣ የሥርዓተ-ትምህርት ባለሙያዎች እና የትምህርት አስተዳደር ባለሙያዎች ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ይህ ፕሮፌሰር አክሊሉ በአማርኛ ቋንቋ አዘጋጅተው ያቀረቡልን መጽሐፍ በዘርፉ ፈር ቀዳጅ ሊሰኝ የሚችል ከመሆኑም ባሻገር በኢትዮጵያ የመምህራን ትምህርትንና የመምህራንን ሙያና ኑሮ ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው እምነቴ ነው፡፡ ስለሆነም ሁሉም የትምህርት ባለ ድርሻ አካላት ይህንን መጽሐፍ እንዲያነቡትና የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ እመክራለሁ።

***ዶ/ር ሰለሞን አርአያ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)***
የትምህርትና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ የመምህርነት ሙያና የትምህርት ጥራት ላይ በተጠናከረ ጥናት የተመሠረተ የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ያሉ ችግሮችን እና በመምህራን ሙያ ላይ ያሉትን ተግዳሮቶች በተደራጁና ጥራት ባላቸው መረጃዎች በጉልህ አቅርቧል። እንዲሁም በኢትዮጵያ የመምህርነት ሙያ ብቃት ማነቆዎች እና የወደፊት መዳረሻው ላይ "ከሙያ-አልባ መምህር ወደ መምህር-አልባ ክፍል" በማለት ሥዕላዊ በሆነ መልኩ ግልጽ አድርጎታል፡፡ በተጨማሪም ለእያንዳንዱ ችግር ሊወሰዱ የሚገባቸውን

የመፍትሔ ሃሳቦች በስፋት አቅርቧል። በመሆኑም መጽሐፉ ደራሲውን የሚያኮራ ተደራሲውንም የሚያነቃ እና ለትውልድ የሚሻገር እንደሆነ አምናለሁ፡፡

***ዶ/ር መስፍን ሞላ ደምሴ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)***
የትምህርት ኮሌጅ፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ

ይህ መጽሐፍ የመምህርነት ሙያ በዓለም ደረጃ አሁናዊ ገጽታ ምን እንደሚመስል በስፋት ለማሳየት ሞክሯል፡፡ በፊንላንድ፣ በደቡብ ኮርያ፣ በጀርመን፣ በጃፓንና ሌሎችንም እንደማሳያ በማቅረብ በመምህርነት ምልመላ፣ ቅድመ-ሥልጠና፣ የሥራ ላይ ልምምድ፣ የተተከታታይ ሙያ ማዳበሪያ ሥልጠና፣ የመምህራን ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች፣ እና በህብረተሰቡና በመንግሥት የሚሰጠው ቦታና ክብር እንደተሞከሮ ቀርቧል፣ ተሞክሮውም መሳጭ ነው። በተቃራኒው በኢትዮጵያ የትምህርት ጥራት በጣም ማሽቆልቆሉን ያሳይና ለዚህም ተጠያቂው መምህሩ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ህብረተሰቡ፣ የትምህርት ቤት ኃላፊዎችና መንግሥት መሆናቸውን ያብራራል። ከምክንያቶቹም መካከል ለመምህራንና ሙያቸው ሲሰጥ የነበረው ቦታ በጣም ዝቅተኛ መሆን፣ የመምህሩ ብቃት ዝቅተኛ መሆን፣ ብቃት የሌላቸውና ያልሠለጠኑ መምህራን ስምሪት፣ የመምህራን ምልመላና ሥልጠና ችግር ያለበት መሆኑ፣ የመምህራን ደመወዝና የኑሮ ሁኔታ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፣ የመምህራን የሥራ ቦታ ምቹ ያለመሆኑ፣ የመምህራን ፍልሰት ከፍተኛ መሆኑ፣ ሥርዓተ ትምህርቱ ጥራት የጎደለው መሆኑ፣ የመምህራን ሥልጠና መርሃ-ግብር በየጊዜው ያለጥናት ተለዋዋጭ መሆኑ፣ የተበላሸ ፖሊሲ አተገባበርና የማስተማሪያ ቋንቋ አተገባበር ዋናዎቹ እንደሆኑ ያሳያል። መጽሐፉ የትምህርት ፍኖተ ካርታ በጥናት መዘጋጀቱንና ይህም ፍኖተ ካርታ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማስቀመጡን ያትታል። ስለሆነም፣ ይህንን መጽሐፍ ስታነቡት አንድም የማታውቁትን እንድታውቁ ይረዳችኋል፣ ሁለትም ስታነቡት እየመሰጠ የመምህራንን ሕይወትና የትምህርት ሥርዓቱን በጉልህ ያሳያችኋል፣ ግንዛቤም ትወስዱበታላችሁ፣ ሶስትም ጥናት ለሚያደርጉ በጣም ጠቃሚ መጽሐፍ እንደሆነ ለመጠቆም ነው። ይህንን መጽሐፍ ካነበባችሁ በኋላ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ህብረተሰቡ፣ የትምህርት ቤት ኃላፊዎችና መንግሥት ትኩረት በመስጠት፤ የመምህራንን ሕይወትና በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት በማሻሻል ረገድ የአቅማችሁን አስተዋፅዖ ታደርጋላችሁ ተብሎ ይጠበቃል።

***ፕሮፌሰር ሙሉጌታ አጥናፉ***
የትምህርትና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

"ተማሪ መጀመሪያ የሚማረው መምህሩ የሚያስተምረውን ሳይሆን መምህሩን ነው"። ፕሮፌሰር አክሊሉ ዳለሎ "የመምህርነት ሙያና የትምህርት ጥራት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ለንባብ ያቀረቡልን መጽሐፍ የአገራችንን የትምህርት ችግር እና መፍትሔውን በስፋትና በጥልቀት አሳይቶናል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ምክንያቱም የትምህርት ጉዳይን በሚያውቁ፤ በሙያው ላይ ብዙ የተመራመሩና ለረጅም ጊዜ ያስተማሩ ብቻም ሳይሆን ሚዛናዊ የሆነና የትምህርት ሥርዓታችንን የሚያሳይ የደራሲውን ማስታወሻ ጭምር ያካተተ ሙሉ መረጃና እውቀት የያዘ፤ አብዛኞቹ ማጣቅሻ ሰነዶች በኢትዮጵያዊያን ምሁራን (ራሳቸውን ፕሮፌሰር አክሊሉን ጨምሮ) የተጻፉ እና በታዋቂ ጆርናሎች የታተሙ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በመሆናቸው ነው። በተጨማሪ ደራሲው የተሳተፉባቸው አገራዊ የትምህርት ሰነድ ዝግጅቶች በስፋት መዳሰሳቸው የመረጃዎቹን ተአማንነት ከፍ ያደርገዋል። አገራችን ለምን የትምህርት ቀውስ ገጠማት ብለን ራሳችንን ብንጠይቅ እንደ እኔ ረጅም ዘመን በማስተማር ሙያ ላይ እንደቆየ መምህር ጥንትም ዛሬም ለትምህርት ሥራና ለመምህርነት ሙያ የተሰጠው ትኩረት እዚህ ግባ የሚባል ስላልሆነ ነው፡፡ አገራችንን እየመሩ ያሉ ትላልቅ ባለስልጣናት እና ምሁራን ጭምር ይህን መጽሐፍ አንብበው ከገጠመን የትምህርት ቀውስ እንድንወጣ የድርሻችንን ለመወጣት የእቅድ መነሻ ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

**ሽመልስ አበበ**
የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) ም/ፕሬዚዳንት

ይህ ጥናታዊ ሥራ፣ በበርካታ አገራዊና የውጭ ጥናታዊ ሥራዎች ዳብሮ፣ በአገረሰባዊ እውቀትና የዘመናት ልምድ ተሸምኖ/ተሰናስሎ፣ ለዓመታት ለተከረቸሙ የችግሮቻችን የወይራ ሳንቃዎች መክፈቻ ቁልፎችን እንካችሁ የሚል ሥራ ነው።፡ የሥራውን ምልዑነት በማጽናት የኢትዮጵያን መጻኢ ትውልድ በዳበረ መሬት ላይ ለመዝራት ግን፣ ቁልፎቹን በቅንነትና በማስተዋል ተቀብሎና ቀርጾ (ወደፖሊሲ ለውጦ)

ፊትለፊት የመጋፈጡ ተግባራዊ ሥራ የሁላችንንም ቅንጅታዊ ርብርብ ይፈልጋል፡፡ ባጭሩም፣ ይህ የፕሮፌሰር አክሊሉ መጽሐፍ ሰሚ ሳይሆን አድማጭ ጆሮዎችን አግኝቶ ወደተግባር ከተመነዘረ፣ ለእኔ፡- ስም፣ ታይትል፣ ሞያ፣ ልምድ እና አገራዊ ስሜት ህብር "Harmony" ፈጥረው የተጣመቁበት ተምሳሌታዊ የትምህርት ጥም ማርኪያና የአገራዊ እድገት ፍኖት ተላሚ ሥራ እንደሆነ አምናለሁ፡ ፡

***ዶ/ር ዳዊት አዲሱ***
የትምህርትና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# ማውጫ ix


| | | |
|---|---|---|
| መቅድም | | xvi |
| መነሻና ጥሪ | | xviii |
| መታሰቢያነቱ | | xxiii |
| ምሥጋና | | xxv |
| **ክፍል አንድ:** | **ሙያ፣ ባለሙያና የመምህርነት ቦታ** | **1** |
| **ምዕራፍ አንድ:** | **መግቢያ** | **2** |
| 1.1. | ጥብቅ ቁርኝት | 3 |
| 1.2. | ከክብር ወደ ክብር ወይስ? | 3 |
| 1.3. | የመምህራን ክብር "መዋዠቅ" ወይስ "ማሽቆልቆል"? ተጠያቂውስ? | 8 |
| 1.4. | የመጽሐፉ ይዘት፣ አደረጃጀትና አቀራረብ | 10 |
| **ምዕራፍ ሁለት:** | **መምህርነት: "ሙያ" ወይስ "ሥራ"?** | **13** |
| 2.1. | መግቢያ | 13 |
| 2.2. | ሙያ እና ባለሙያ | 13 |
| 2.3 | መምህርነት፣ "ሙያ" ወይስ "ሥራ"? | 15 |
| 2.4. | የመምህርነት ሙያ ልዩ ባህርያት | 17 |
| 2.5. | በመምህርነት ዙሪያ ዘመን ተሻጋሪ ክርክሮች | 23 |
| 2.6. | የመምህርነት ሙያ ውስጣዊ ተግዳሮቶች | 24 |
| 2.7. | መደምደሚያ | 27 |
| **ምዕራፍ ሦስት:** | **የመምህርነት ሙያ አሁናዊ ሁኔታ: ዓለምአቀፋዊ ቅኝት** | **29** |
| 3.1. | መግቢያ | 29 |
| 3.2. | ምልመላና ልየታ | 31 |
| 3.3. | የቅድመ-ማስተማር ዝግጅት/ሥልጠና | 36 |
| 3.4. | የጀማሪ መምህራን የሥራ ላይ ልምምድ (Induction) | 45 |
| 3.5. | ተከታታይ የሙያ ማዳበሪያ ሥልጠና | 47 |
| 3.6. | የሥራ ቦታና ሁኔታ | 49 |
| 3.7. | ደመወዝና ጥቅማጥቅም | 50 |
| 3.8. | የመምህራን አሠልጣኞች ዝግጅትና ስምሪት | 54 |
| 3.9. | የአፍሪካ ሁኔታ | 55 |
| 3.10. | መደምደሚያ | 58 |
| **ክፍል ሁለት:** | **የመምህርነት ሙያና የትምህርት ጥራት** | **61** |
| **ምዕራፍ አራት:** | **የትምህርት ጥራትና የመምህራን ድርሻ** | **62** |
| 4.1. | መግቢያ | 62 |
| 4.2. | ስለትምህርት ጥራት በጥቂቱ | 63 |
| 4.3. | የትምህርት አግባብነትና ጥራት መዋዠቅ: የሥርዓቱ ችግር ወይስ የባህልና ታሪክ ጫና? | 64 |
| 4.4. | የትምህርት ጥራት ምሰሶዎች | 68 |
| 4.5. | የትምህርት ጥራት እንዴት ይረጋገጣል? | 70 |
| 4.6. | የትምህርት ጥራት መስፈርቶች | 72 |
| 4.7. | የትምህርት ጥራት ልኬት መርሆች | 74 |
| 4.8. | የትምህርት ጥራትና ሁለንተናዊ ልማት: እውን ይዛመዳሉ? | 76 |
| 4.9. | የትምህርት ጊዜ ርዝመትና ፋይዳው | 81 |
| 4.10. | ጥራት ያለው መምህር ማንነት | 83 |
| 4.11. | የትምህርት ጥራት ጉድለትና መዘዞቹ | 86 |
| 4.12. | የትምህርትን ጥራት ለመረዳት፣ ለማሻሻልና ለመገምገም | |

| | | |
|---|---|---|
| | የሚያግዝ ማዕቀፍ | 92 |
| 4.13. | የጥራት ተምሳሌት የሆኑ አገሮችና ተሞክሮዎቻቸው | 97 |
| 4.14. | የመምህራን ብቃት በተማሪዎች እይታ | 98 |
| 4.15. | መደምደሚያ | 100 |
| **ምዕራፍ አምስት:** | **የመምህርነት ሙያና የትምህርት ጥራት በኢትዮጵያ: ታሪካዊና አሁናዊ ዳራ** | **102** |
| 5.1. | መግቢያ | 103 |
| 5.2. | ጥቂት ስለሙያዎች በኢትዮጵያ | 109 |
| 5.3. | የመምህርነት ሙያ በቅድመ ዘመናዊ ትምህርት | 109 |
| 5.4. | የዘመናዊ ትምህርት መባቻና የመምህርነት ሙያ | 117 |
| *5.4.1.* | *የሚሲዮናውያን ሁለተኛ ሙከራ* | *117* |
| *5.4.2* | *አፄ ቴዎድሮስና የመጀመሪያው ትምህርት ቤት!* | *119* |
| *5.4.3.* | *አጼ ምንሊክና የተሳካው ሙከራ* | *122* |
| *5.4.4.* | *የአጼ ኃይለሥላሴ ትምህርትን የማስፋፋት ሙከራዎችና የሚስዮናውያን ሚና* | *125* |
| 5.4.5. | መምህራንና ሙያቸው በነጻነት ማግስት | 135 |
| 5.5. | የመምህርነት ሙያ በሶሻሊስቱ መንግሥት (ደርግ) ዘመን | 142 |
| 5.6. | የመምህርነት ሙያ ከኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት እስከ ዛሬ | 146 |
| 5.7. | የመምህራን አሠልጣኞች ዝግጅት | 149 |
| 5.8. | የመምህራን ጥራት: እውን የቀድሞ መምህራን ይሻሉ ነበርን? | 154 |
| 5.9. | የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና እድሣት | 156 |
| 5.10. | መደምደሚያ | 158 |
| **ክፍል ሦስት:** | **የኢትዮጵያ ትምህርት ጥራት ማነቆዎች** | **161** |
| **ምዕራፍ ስድስት:** | **በቂ ሙያዊ ዝግጅትና ፍላጎት የሌላቸው መምህራን ስምሪት** | **162** |
| 6.1. | መግቢያ | 162 |
| 6.2. | የችግሩ ዳራ: የሠለጠኑ መምህራን እና ርዕሰ መምህራን እጥረት | 163 |
| 6.3. | የዕጩ መምህራን ምልመላ፣ ዝግጅትና ስምሪት | 172 |
| *6.3.1.* | *የተማረ ሁሉ ያስተምር! እንዴት አድርጎ?* | *172* |
| *6.3.2.* | *ዕጩ መምህራንን ያለፍላጎትና ዝንባሌ መመደብ* | *175* |
| *6.3.3.* | *"ባጣ ቆየኝ" እና መዘዙ* | *178* |
| *6.3.4.* | *ጥራት-ጉዳይ አዙሪት: ከደካማ ተማሪነት ወደ ደካማ አስተማሪነት* | *181* |
| *6.3.5* | *እውቀትን ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የማቀናጀትን አቅም ማጣት* | *184* |
| 6.4. | መደምደሚያ | 185 |
| **ምዕራፍ ሰባት:** | **ከአሰለጣጠን ሂደት ጋር የተቆራኙ ክፍተቶች** | **186** |
| 7.1. | መግቢያ | 186 |
| 7.2. | ዕጩ መምህሩን ማን ያስተምር? "ያልሰጡትን መጠየቅ?" | 186 |
| 7.3. | በመምህራን ዝግጅት ባለድርሻ አካላት መካከል ያለው መስተጋብር: ፉክክር ወይስ ትብብር? | 188 |
| 7.4. | ተማሪ-ተኮር የማስተማሪያ ዘዴን ተግባራዊ አድርግ!፤ ያለድጋፍ የሚኾንደኅድ ትዕዛዝ? | 190 |
| 7.5. | የዕጩ መምህራን ተቋማዊ ትኩረት ማጣት | 192 |
| 7.6. | መደምደሚያ | 194 |
| **ምዕራፍ ስምንት:** | **የነባር መምህራን ፍልሰትና የሥነምግባር ችግሮች** | **195** |
| 8.1. | መግቢያ | 195 |
| 8.2. | የሠለጠኑ መምህራን ፍልሰት፣ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ? | 196 |
| 8.3. | "እያሉ የሌሉ" መምህራን | 201 |
| 8.4. | የመምህራን ሙያዊ ሥነምግባር ጉድለት | 205 |

| | | |
|---|---|---|
| 8.5. | ዲግሪ በአራት ሳምንት! የክረምት ትምህርትና ሕጸጾቹ | 207 |
| 8.6. | ያልተሳካ የሙያ ላይ አቅም ግንባታ | 208 |
| 8.7. | መደምደሚያ | 210 |
| **ምዕራፍ ዘጠኝ:** | **የተማሪው ሁኔታና የመምህሩ "ፍዳ"** | **211** |
| 9.1. | መግቢያ | 211 |
| 9.2. | የተማሪና መምህሩ ግንኙነት መሻከር | 212 |
| 9.3. | የዘመኑ ፈተና፤ ፍላጐትና ተነሳሽነት የሌለው ተማሪ | 215 |
| 94. | "ትምህርት ድሮ ቀረ!"፣ "ትምህርት የፋራ ነው!" | 218 |
| 9.5. | መደምደሚያ | 223 |
| **ምዕራፍ አሥር:** | **ከትምህርት ሥርዓቱና አስተዳደሩ ጋር የተቆራኙ ችግሮች** | **224** |
| 10.1. | መግቢያ | 224 |
| 10.2. | ጥራትና አግባብነት የሌለው ሥርዓተ ትምህርት፡ መምህሩ ምን ያድርግ? | 227 |
| 10.3. | የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራን ትኩረት ማጣት | 232 |
| 10.4. | አሃዳዊ ትምህርትና የመምህሩ ፍዳ | 234 |
| 10.5. | አቅም ያላቸው መምህራን በየትኛው የትምህርት እርከን ይመደቡ? | 236 |
| 10.6. | የሁለተኛ ደረጃና የዩኒቨርሲቲ መምህራን ዝግጅት ጉድለቶች | 237 |
| 10.7. | ሙያ ነክ ኮርሶች ዙሪያ ያለው ውዝግብ | 243 |
| 10.8. | የተግባር ሥልጠና (ፕራክቲከም) ሕጸጾች | 248 |
| 10.9. | ተማሪዬ ሆይ፤ ለምን ቀረህ? የመምህሩ ቤት ለቤት የመዞር ግዴታ! | 250 |
| 10.10. | አንድ-ለአምስት፣ የግብ ስምምነትና ለ 'ውጤት አብቃ' መርሆች | 252 |
| 10.11. | "አምልኮተ" ብሔራዊ ፈተናና የትምህርት ጥራት | 254 |
| 10.12. | ፕላዝማ፤ የጥራት ኢጋዥ ወይስ? | 257 |
| 10.13. | የኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች "እንደ አሸን መፍላት" እና የትምህርት ጥራት | 259 |
| 10.14. | ሙያዊ ብቃትና ሥነምግባር የሌለው የትምህርት አመራር | 261 |
| 10.15. | መደምደሚያ | 263 |
| **ምዕራፍ አሥራ አንድ:** | **የመምህሩ የሥራና የኑሮ ሁኔታ** | **264** |
| 11.1. | መግቢያ | 264 |
| 11.2. | ከወር ወር የማያሻግር ደመወዝ | 266 |
| 11.3. | ጥበብ የጎደለው የደረጃ ዕድገትና ማትጊያ ሥርዓት | 268 |
| 11.4. | ጥራት የሌለው የሥራ ቦታና ምቾት የጎደለው የሥራ ሁኔታ | 272 |
| 11.5. | ማህበረሰቡ ስለሙያው ያለው እይታ | 275 |
| 11.6. | መደምደሚያ | 283 |
| **ክፍል ሰፊት:** | **ቋንቋና የትምህርት ጥራት** | **285** |
| **ምዕራፍ አሥራ ሁለት:** | **የማስተማሪያ ቋንቋ፡ የመምህሩ የጎን ውጋት?** | **286** |
| 12.1. | መግቢያ | 286 |
| 12.2. | ጥቂት ስለ መማሪያ-ማስተማሪያ ቋንቋዎች | 288 |
| 12.3. | "እንግሊዝኛን በአማርኛ ማስተማር!" | 289 |
| 13.4. | ቋንቋና የመማር-ማስተማር ዘዴዎች አጠቃቀም | 294 |
| 12.5. | ችግሩ እውን የቋንቋ ወይስ የሃሳብ ድህነት? | 296 |
| 12.6. | መደምደሚያ | 298 |
| **ምዕራፍ አሥራ ሦስት:** | **ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ፡ ፔዳጎጂያዊ ወይስ ፖለቲካዊ ጉዳይ?** | **299** |
| 13.1. | መግቢያ | 299 |

13.2. የአገር ውስጥ ቋንቋ(ዎች) መጠቀም፡ ጥቅሙና ተግዳሮቶቹ 301
13.3. የመማሪያ-ማስተማሪያ ቋንቋ አገራዊ የማድረግ ጥረቶች 305
13.4. የመማሪያ-ማስተማሪያ ቋንቋን አገራዊ ከማድረግ ጋር የተያያዙ ችግሮች 307
13.5. ውኾንብሩ እንዴት ይጥራ? 314
13.6. መደምደሚያ 317

**ክፍል አምስት: የዕጩ መምህራንና የመምህራን አሠልጣኞች ዝግጅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (በጸሐፊው ማስታወሻ ላይ የተመሠረተ) 322**

**ምዕራፍ አሥራ አራት፡ ጉዞ ከተማሪነት ወደ መምህራን አሰልጣኝነት 323**
14.1. መግቢያ 323
14.2. ጉዞ ከሌጌ/ዊሾኣሞ ወደ አአዩ ስድስት ኪሎ ግቢ 324
14.3. ጂኦግራፊ በምርጫ 325
14.4. ረዳት ምሩቅ በካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ዲፓርትመንት 328
14.5 መደምደሚያ 335

**ምዕራፍ አሥራ አምስት፡ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ዝግጅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 336**
15.1. መግቢያ 336
15.2. አሥራ ስምንት ክሬዲት በጅምላ 337
15.3. የዘርፎች (Streaming) መጀመር 339
15.4. የመምህራን ትምህርት ሥርዓት ተሃድሶ 343
5.5. ድምበማ (ድሕረ-ምረቃ በማስተማር) 349
15.6. ባችለር ዲግሪ በትምህርት (ባዲበት) 352
15.7. የትምህርት ፍኖተ ካርታና አዲሱ ፖሊሲ 353
*15.7.1. ዋና ዋና ችግሮች 356*
*15.7.2. የመፍትሔ አቅጣጫዎች 358*
*15.7.3. ከፍኖተ ካርታ ወደ ትምህርት ፖሊሲ 362*
*15.7.4. የአጠቃላይ ትምህርት አዋጅ 364*
*15.7.5. የመምህራን ዝግጅትና ሥልጠና ማዕቀፍ 371*
*15.7.6. የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ እና የ2ኛ ደረጃ መምህራን አቅም ግንባታ 375*
15.8. መደምደሚያ 377

**ምዕራፍ አሥራ ስድስት፡ ምን ማድረግ እንችላለን? መደምደሚያ እና ሙያዊ ምክረ-ሃሳብ 379**
16.1. መግቢያ 381
16.2. ቁጭታችንን ወደ ገንቢ ኃይል እንለውጥ! 381
16.3. የመምህራን ምልመላና ዝግጅት 384
16.4. የመምህራን ስምሪት፣ ክትትልና ድጋፍ 392
16.5. የመምህሩ ሥራና ኑሮ 394
16.6. ሙያዊ እይታና ክብር 398
16.7. የገቢ ማግኛ እና የመሰብሰብያ መንገዶችን ማብዛት 402
16.8. የትምህርትና የመግባቢያ ቋንቋዎች ፖሊሲ መከለስ 403
16.9. ራስን በራስ የመቆጣጠር ባህል ማዳበር 408
16.10. የዘርፉን ምርምር ማጠናከር 410
16.11. ማጠቃለያ 410

የአማርኛ ዋቢዎች 413
የእንግሊዝኛ ዋቢዎች 418
በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ፋኩልቲ/ኮሌጅ በዲንነት ያገለገሉ ምሁራን 446

**ሣጥኖች**


| | | |
|---|---|---|
| ሣጥን 3.1፡ | The status of the teaching profession in Korea | 34 |
| ሣጥን 3.2፡ | የጀርመን ተሞክሮ፣ ችሎታ ካለህ አስተማሪ ሁን! | 43 |
| ሣጥን 3.3፡ | የተማሪ ውጤታማነት መሠረቶች | 51 |
| ሣጥን 4.1፡ | አንድን አገር ለማፍረስ "ፍቱን" መንገድ | 90 |
| ሣጥን 5.1፡ | የጥንታዊ ትምህርት መምህራን፤ የተከታታዩ ትውልድ ባለውለታዎች! | 110 |
| ሣጥን 5.2. | የደቡቡና ምዕራቡ የአገራችን ክፍል እንዴት የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ ሃይማኖቶች በፈቃዱ እንደተቀበለ? | 119 |
| ሣጥን 5.3. | በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ገጠር መሠረተ ትምህርት መስፋፋት | 131 |
| ሣጥን 5.4. | Economic-religious Mission Stations | 134 |
| ሣጥን 5.5፡ | Best practices of the Lab School and the lessons learnt | 139 |
| ሣጥን 5.6፡ | የመምህርነት ሙያ በሰሻሊስት ሥርዓት ወቅት (1974–91 እአአ) | 143 |
| ሣጥን 5.7. | የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ከመመረቃቸው በፊት ለአንድ ዓመት እንዲያስተምሩ ሊገደዱ ነው | 148 |
| ሣጥን 5.8፡ | የመጀመሪያው የመምህራን ትምህርት ተቋማት ሥርዓተ ትምህርት | 151 |
| ሣጥን 5.9፡ | የመጀመሪያው የቅድመ መደበኛ መምህራን ማሠልጠኛ ማዕከል | 152 |
| ሣጥን 8.1: | መምህር፣ ከፊል አርሶ አደር/አርብቶ አደር፣ ከፊል ነጋዴ፣ ከፊል መምህር የመሆን ዝንባሌ | 204 |
| ሣጥን 10.1፡ | የኢትዮጵያ ትምህርት ጥራት ማነቆዎች | |
| ሳጥን 10.2: | 'I myself was also a culprit': The confession of a former university lecturer | 231 |
| ሳጥን 13.1፡ | ኢትዮጵያም እንደ ቅኝ ተገዢዎቹ... | 303 |
| ሣጥን 13.2፡ | በቋንቋ ዙሪያ የሚታየው የልሂቃን መቆራቆዝ | 308 |


**ምስሎች**


| | | |
|---|---|---|
| ምስል 3.1: | የዕጩ መምህራን ምልመላ፣ ዝግጅትና ስምሪት ቁርኝት | 31 |
| ምስል 3.2፡ | የቅድመ ሥልጠና የመማር-ማስተማር ሂደትና የመምህሩ ድርሻ | 37 |
| ምስል 16.1፡ | በቢሾፍቱ ከተማ በሚገኝ የመምህራን አደባባይ ለመምህራን ክብር የተገነባ ሐውልት | 380 |


**ሠንጠረዦች**


| | | |
|---|---|---|
| ሠንጠረዥ 5.1፡ | የመምህራን ቁጥር እድገትና የሚሲዮናውያን አስተዋጽዖ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ከ1965 እስከ 1975 | 130 |
| ሠንጠረዥ 6.1.: | ዕጩ መምህራን የመምህርነትን ሙያ የመረጡበት ዋና ምክንያት በተመለከተ | 177 |
| ሠንጠረዥ 8.1: | አሁን ባለው ሁኔታ የመምህራን ሥራ የመልቀቅ ፍላጎት | 199 |
| ሠንጠረዥ 14.1፡ | ከመምህርነት ሙያ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ኮርሶች | 326 |
| ሠንጠረዥ 14.2፡ | የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ይዘት | 331 |
| ሠንጠረዥ 15.1፡ | የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ዝግጅት ሂደት | 336 |
| ሠንጠረዥ 15.2፡ | በመትሥተ የቀረበ ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሥልጠና ይዘት | 344 |

ሠንጠረዥ 15.3፡ የድምበማ ኮርሶች 350
ሠንጠረዥ 15.4፡ የባዲበት መርሃ-ግብር ኮርሶች 353

ቻርት 1፡ የትምህርት ጥራት ለመረዳት፣ ለመገምገምና ለማሻሻል
የሚያግዝ ማዕቀፍ (Framework) 93

## መቅድም

የአንድን አገር የትምህርት ሥነምህዳር የሚቀርጹና የትምህርቱን ጥራት የሚወስኑ በርካታ ነገሮች መኖራቸው የማይታበል ነው። ከነዚህ ነገሮች መካከል ደግሞ ብቃት ያላቸው መምህራን ድርሻ ወደር የለሽ መሆኑ እንዲሁ አሌ የሚባል አይደለም። ይህ በፕሮፌሰር አክሊሉ ዳለሎ የቀረበልን መጽሐፍ በመምህርነት ሙያና የትምህርት ጥራት መካከል ያለውን ቁርኝት በብዙ መረጃ በመተንተን ጥራት ያለው መምህር በሌለበት ጥራት ያለው ትምህርት መፈለግ "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" ከመሆን አይዘልም በማለት ይሞግታል።

ከፕሮፌሰር አክሊሉ ጋር በቅርብ አብሬው ሰርቼአለሁ፡፡ በተለያዩ መድረኮች ላይም በትምህርት-ነክ ጉዳዮች ተወያይተናል። የመምህርነት ሙያ በአገራችን እያሽቆለቆለ በመሄዱ በከፍተኛ ቁጭትና ተቆርቋሪነት ሀሳቡንና ስሜቱን ለሚመለከታቸው ክፍሎች ሲያጋራም ቆይቷል። በዚህ መጽሐፍ ዝግጅትም የዳሰሳ ጥናትና በመስኩ ምርምር በማካሄድ የመምህርነት ሙያ በሀገራችን የደረሰበትን ደረጃና ክብር በመተንተን ቁልጭ አድርጐ በቀላል ቋንቋ ለአንባቢ አስቀምጧል።

ከፐሮፌሰር አክሊሉ ጋር በቅርብ ጊዜ በአገር አቀፍ ጀረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደው የኢትዮጵያ ትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታ ዝግጅት አብረን ተሳትፈናል። በዚህም ጊዜ እሱ የመምህራን ልማትና ሥልጠና ዘርፍ የምርምር ቡድን መሪ በመሆን ኃላፊነቱን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል የተወጣ ምሁር መሆኑን አለማንሳት ንፉግነት ነው። እንደሚታወቀው ሁሉ በኢትዮጵያ ትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታው ላይ የቀረቡት ምክረ-ሃሳቦች በተከታታይ በወጡት የሀገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፓሊሲና ሕግ ላይ ያደረጉት ተፅዕኖ ቀላል አይደለም። ይህ እውነታ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በስፋትና በጥልቀት መዳሰሱ የመጽሐፉን ጠቀሜታ ዘመን ተሻጋሪ ያደርገዋል።

ጸሐፊው በመምህርነት ሙያ ዙሪያ የሚስተዋለው አሳሳቢ ሁኔታ በአስቸኳይ መፍትሔ ተፈልጐ ካልተስተካከለ የትምህርት ጥራትም ሆነ አገሪቷ ልትደርስበት ካለመችው የልማትና ብልጽግና ማማ መድረስ እንደማትችል በማያሻማ መልክ አቅርቧል። ዘርፉ ጥገናዊ ሳይሆን ሥር-ነቀል የፖሊሲና የአመለካከት ለውጥ እንደሚያስፈልገውም ተመላክቷል። በእርግጥ የአንድ አገር የትምህርት ጥራት እና የትውልድ ግንባታ የቤተሰብ፣ የተማሪዎች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ሚና እንዳላቸው ቢታወቅም መምህራን የአንበሳውን ድርሻ እንደሚወስዱ በመጽሐፉ በሚገባ ተሰምሮበታል።

የመምህርነት ሙያ እንዴትና በምን መልክ በአገራችን መሻሻልና መደራጀት አለበት ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄም ጸሐፊው መፍትሔውን ከመተንተንና ከመጠቆም ወደ ኋላ አላለም። ጸሐፊው በዚህ ላይም የተለያዩ የጥናትና የምርምር ውጤቶችን በማጣቀስ በመምህራን ዝግጅት ብሎም በትምህርት ጥራት ውጤታማ የሆኑ አገራትን ልምድ በመውሰድና ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማቀናጀት ምን ምን ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራትና ምን መሆን እንዳለበት አመላክቷል። ለምሳሌ የአገራችንን እና ዓለምአቀፉን ነባራዊ ሁኔታን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የመምህራን ምልመላ፣ ዝግጅት፣ ጥቅማጥቅም፣ ተሳትፎ፣ እድገት፣ የሥራ ደህንነት እና የትምህርት መማሪያ ቋንቋ የመሳሰሉት ጉዳዮች ሊኖራቸው ስለሚገባው ቅርጽና ይዘት ዝርዝር የመፍትሔ ሃሳብ አቅርቧል።

የፕሮፌሰር አክሊሉ መጽሐፍ ከተጠቀምንበት ለመምህርነት ሙያ የፖሊሲ ግብዓት በመሆን መሠረታዊና ዘለቄታ ያለው ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችልና ለአገራችንም ብሩህ ተስፋ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። ትምህርት ለአንድ አገር ሰላም፣ ዕድገትና ብልጽግና መሠረት በመሆኑ በዚህ መጽሐፍ የተዳሰሱ ቁም ነገሮች ልዩ ትኩረትና የቅድሚያ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል።

***ሎሬት ፕሮፌሰር ጥሩሰው ተፈራ***
የትምህርትና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## መነሻና ጥሪ

> "የትምህርት መስፋፋትና ጥራት ደረጃ፤ በዛሬው አመለካከት፤ በአገሮች መካከል ሀብታምና ደሃውን የመለያ መስፈርት ተደርጎ መቆጠርና መታመን ደረጃ ደርሷል" (አክለሉ ሀብቴ፣ 2010 ዓ/ም፣ ገጽ 8)።
>
> "ሀገርን ለመገንባት እና ለውጥ ለማምጣት፤ ከትምህርት በላይ ዐቅም ሊሰጥ የሚችል የሰው ልጆች መሣሪያ የለም ... ሀገር መምሰል የምትፈልገውን እና ማምጣት የምትፈለገውን ለውጥ ለመፍጠር፤ ከልጅነት ዕድሜ ጀምሮ የሚከተብ ትምህርት፤ ከሁሉም የገዘፈ አስተዋፅዖ አለው" (ዐቢይ፣ 2015 ዓ/ም፣ ገጽ 221-222)።
>
> "… without teaching there would be no other professions" (Jacques, 2005, p.15)፡ "ትምህርት ከሌለ ሌሎች ሙያዎች ሊኖሩ አይችሉም"።

የዚህ መጽሐፍ መነሻ ቁጭት ነው፡፡ ቁጭቱም በሁለት ደረጃዎች ሊገለጽ ይችላል፡፡ አንደኛው አገራችን ጥሩ ታሪክና ባህል ያላት ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በቴክኖሎጂና በምጣኔ ሀብት ዕድገት የዓለማችን ጭራ ሆና መገኘቷ ነው፡፡ በሌሎች አገራት ለቴክኖሎጂ ልማት፣ ስርጭትና የምጣኔ ሀብት ዕድገት ዘመናዊ ትምህርት ወደር የለሽ አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡ በእኛ አገር የዘመናዊ ትምህርት ዕድሜው አጭር መሆኑ የማይካድ ቢሆንም በዚህ ጊዜ ማድረግ የሚችለውንና የሚገባውን አላደረገም የሚል እምነት የመጀመሪያው ቁጭት ምክንያት ነው፡፡

ክቡር ዶ/ር ከበደ ሚካኤል የአገራችን ድህነት ሥረ-መሠረቱ የዜጎቿ የሃሳብ ድህነት መሆኑን አስረግጠው ካሳዩ በኋላ "አሳባችንን ኃይለኛ ልናደርገው የምንችለው ደግሞ ጉልበታችንን እርባና ለሌለው ነገር ማባከናችንን ትተን እነዚህን ለአገራችን ዋኖች ጉዳዩች የሆኑትን ነገሮች ብቻ ባሳባችን ውስጥ በማውጣትና በማውረድ የሚበጀውንም መንገድ ለማግኘት ስንል ከእነዚሁ ጉዳዮች አዲስ ሀሳብ እየሰጡን ሊረዱን የሚችሉትን መፃሕፍት በማንባብ ነው" በማለት ይመክራሉ (ከበደ፣ 1973 ዓ/ም፣ ገጽ 99-100)። በአሁኑ ወቅት "ለአገራችን ዋኖች ጉዳዩች" ከሆኑትና እድገታችንን ከሚያሰናክሉ ነገሮች መካከል አንዱ የትምህርት ጥራት ጉድለት እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም። ስለሆነም ይህ መጽሐፍ የጸሐፊውን ቁጭት ከማጋራት ባሻገር በጉዳዩ ላይ ለሚደረግ አገራዊ ምክክርና የመፍትሔ ፍለጋ ጥረት የራሱን አስተዋጽዖ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል።

ሁለተኛው ቁጭት ሙያዊ ነው፡፡ የመምህርነት ሙያ ለአገር ግንባታ በአጠቃላይና በተለይ ደግሞ ለቴክኖሎጂ ልማት፣ ስርጭትና የምጣኔ ሀብት ዕድገት መሠረት እንደሆነ ይታመናል፡፡ የማንኛውም አገር የትምህርት ጥራት ከመምህሩ ጥራት ሊልቅ እንደማይችልም እንዲሁ ይታመናል፡ "ብቃት ያላቸው መምህራን በሚፈለገው መጠን ካልተገኙ በስተቀር ምንም ቢደረግ በቀለም ትምህርቱ ጥራት ላይ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አይቻልም" (መለስ፣ 2009 ዓ/ም፣ ገጽ 330)፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ዛሬ በአገራችን ለሚታየው ዝቅተኛ የቴክኖሎጂ ልማትና የምጣኔ ሀብት ዕድገት የመምህራን የብቃትና ሙያዊ መሰጠት (commitment) አናሳነት አንዱ ምክንያት ነው፡፡

በአገራችን ብቁ መምህራን እንዳይፈጠሩና የተፈጠሩትም እንዳይቆዩ ያደረጉ በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከምክንያቶቹ ሁሉ እጅግ ጎጂ የሆነው ማህበረሰቡ ለመምህራን የሚሰጠው ዝቅተኛ ቦታና ክብር ነው፡፡ ባለሙያውን እየናቁና እያጥላሉ የሙያውን

ትሩፋቶች (የቴክኖሎጂ ልማትንና የምጣኔ ሀብት ዕድገትን ጨምሮ) በእጅጉ የመፈለግ አባዜ በአገራችን ከተንሰራፋ ውሎ አድሯል፡፡ይህ የሁለተኛው ቁጭት ምክንያት ነው፡፡

የመጽሐፉ ትኩረት የመምህርነት ሙያ በኢትዮጵያ ያለፈበትን ጎዳናና አሁን ያለበትን ሁኔታ መዳሰስና ሁኔታው በትምህርት ጥራት ላይ ያለውን እንድምታ ማሳየት ነው። የመጽሐፉ መነሻ ቁጭት ቢሆንም ይዘቱ በተቻለ መጠን ከልክ ካለፈ ስሜታዊነት የፀዳና በመረጃ የተደገፈ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህ ሲባል ግን ሐቅና ስሜት ሊነጣጠሉ ይችላሉ ወይም መነጣጠል አለባቸው ለማለት ሳይሆን ለችግሮቻችን የቀረቡ የመፍትሔ ሃሳቦች በሙሉ ዓለምአቀፋዊ ተሞክሮዎችንና ሙያዊ ትንታኔን መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን ለማሳየት ነው ፡፡

ለመጽሐፉ መነሻ የሆነው የመጀመሪያው ቁጭት (የአገራችን የዓለም ጭራ ሆና የማየት ቁጭት) የሁሉም ኢትዮጵያዊ ቁጭት ነው ተብሎ ይገመታል፡፡ የመምህራንና የሙያቸው ክብር ማጣት ግን የሁሉም ኢትዮጵያዊ ቁጭት የሆነ አይመስልም፡፡ ይህ ደግሞ አስገራሚና አሳዛኝ ነው፡፡ ምክንያቱም ለአገራችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ማደግና በምጣኔ ሀብት ልቆ መገኘት የሚጨነቅ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለትምህርት ጥራት መጨነቅ ይጠበቅበት ነበርና ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ለትምህርት ጥራት የሚጨነቅ ሁሉ ለመምህራን ጥራት መጨነቅ አለበት፡፡ ጥራት ያለው መምህር ማግኘት ከተፈለገ ደግሞ መምህሩንና ሙያውን ማክበር የግድ ይላል፡፡ ማህበረሰቡ በናቀው ሙያ ውስጥ ማን ተሳታፊ መሆን ይፈልጋል? በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ሙያውን የተቀላቀለስ ቢሆን እንዴት እዚያ እንዲቆይ ይጠበቃል? ይህ የሚታሰብ አይደለም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ለመምህራንና ለሙያቸው የሚሰጠውን ዝቅተኛ ቦታ እያዩ የአገራችን ህዳሴ ይመጣል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው፡፡ መምህራኑን የማያከብር አገር ቁልቁል ሲወርድ እንጂ ሲያድግ አልታየም፤ አይታይም፡፡ በ20ኛውና በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት በሚያስደምም የህዳሴ ጎዳና የተራመዱና እየተራመዱ ያሉ አገራት ለመምህራን የተለየ አክብሮት ያላቸው ናቸው፡፡ ለዚህ ጃፓን፣ ደቡብ ኮሪያና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ቬይትናም ምስክሮች ናቸው፡፡

ስለሆነም ይህ መጽሐፍ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የአክብሮት ጥሪ ያቀርባል፡፡ አራት ወገኖች ግን በተለየ መልኩ ትኩረታቸውን እንዲሰጡና ዛሬ-ነገ ሳይሉ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የመፍትሔ ሃሳቦች እንዲተገብሩ ጥሪ ተደርጎላቸዋል፡፡ ከእነዚህ የመጀመሪያዎቹ ወላጆች ናቸው፡፡ ማንኛውም ወላጅ ልጁ በእውቀት፣ በአመለካከትና በክህሎት ከፍ ብሎ እንዲያድግለት ይፈልጋል፡፡ ይህ የሚጠበቅና ተፈጥሮአዊ ነው። ወላጅ ሊገነዘብ የሚገባው “መራራ እውነት” ግን መምህራንና ሙያቸው በተዋረዱበት አገር ለልጆቻቸው የሚመኙትን ማግኘት እንደማይችሉ ነው፡፡ ለልጆቹ መልካሙን ሁሉ የሚመኝ ወላጅ ያለው አማራጭ አንድ ነው፤ ለመምህራናቸው አክብሮትና “ከንፈር ከመምጠጥ” ያለፈ ድጋፍ ማድረግ፡፡

ሁለተኛው ልዩ ጥሪ የቀረበለት መንግሥት ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት አገራችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ መጥቃ ማየት ይፈልጋል፡፡ ይህንኑ ለማሳካት ሲተጋም ይታያል። በብሶት ውስጥ የሚኖሩ መምህራን በሞሉበትና ለልጆቻቸው የዕለት ኑሮ የሚጨነቁ ምሁራን በሚበዙበት አገር ሳይንሳዊ ምርምርና ፈጠራ ላይ አእምሮኣቸውን የሚያውሉ ተመራማሪዎችና ለእንደዚህ ዓይነት ምርምርና ፈጠራ የሚዘጋጁ ተማሪዎችን መጠበቅ ከንቱ ቅዠት ይሆናል፡፡ መንግሥት መምህራንንና ሙያቸውን የአገሪቱ የፖሊሲ ማዕካል አድርጎ ቢሠራ ለሚመኘው የቴክኖሎጂ ልማትና የምጣኔ ሀብት ዕድገት ጠንካራና አስተማማኝ መሠረት ይጥላል፡፡ ፍሬውንም ቀስ በቀስ ማየት ይጀምራል፤ ትምህርት ዛሬ ዘርተን በአራት ወር የምናጭደው ሰብል ስላልሆነ።

በሦስተኛ ደረጃ ጥሪ የቀረበላቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጅቶች አገራችን ሁለንተናዊና ዘለቄታ ያለው ልማት እንዲኖራት ርዕይ ይዘው የሚሠሩ ናቸው፡፡ ዘለቄታ ያለው ልማት መሠረቱ ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርት ነው፡፡ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ጥራት ያለው ትምህርት ጥራት ካለው መምህር ውጪ የሚታሰብ አይደለም፡፡ ስለሆነም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡ የመፍትሔ ሀሳቦች መካከል ከእነርሱ ተልዕኮና ርዕይ ጋር ዝምድና ያላቸውን እየለዩ የራሳቸውን አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ በአክብሮት ተጋብዘዋል፡፡

በአራተኛ ደረጃ የተጋበዙት የሙያው ባለቤቶች ናቸው፡፡ ይህም መምህራንንና ከሙያው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን (ርዕሰመምህራን፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ ወዘተ.) የሚያካትት ነው፡፡ የመምህርነት ሙያ እንዲከበር የሙያው ባለቤቶች ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው ሊታወቅ ይገባል፡፡ ሌላው ሙያውን እንዲያከብር ከተፈለገ የሙያው ባለቤቶች ሙያው የሚጠይቀውን ሥነምግባር የተላበሱ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ይህ ካልሆነ “ባለቤቱ የናቀው አሞሌ ....” ይሆናል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም መጽሐፉ የሙያው ባለቤቶች ሊያደርጓቸው የሚገባቸውን በርካታ ነገሮች ያቀርባል፡፡ መምህራንና ከሙያው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ወገኖች የየራሳቸውን ድርሻ ተወጥተው ከወላጅ፣ ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተቀረውን ቢጠብቁ ትክክል ይሆናል፡፡

አራቱም ወገኖች ሀሳባቸውንና ተግባራቸውን አቀናጅተው ከተጉ የአገራችን መምህራንና ሙያቸው ተገቢውን ቦታና ክብር ያገኛሉ፤ ሁላችንም የምንመኘው የአገራችን ህዳሴም ይፈጥናል፤ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!

**አክሊሉ ዳለሎ (ፕሮፌሰር)**
ሐምሌ 2017 ዓ/ም፣ አዲስ አበባ

"ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያን የመምህራን ሙያና የመምህራን አሠለጣጠን በተለየ አቀራረብና በድፍረት ፍንትው አድርጎ በአገራዊ ቋንቋ በማቅረቡ በአይነቱ የተለየ ምናልባትም የመጀመሪያው ሊያደርገው ይችላል፡፡"

*ዶ/ር ሰለሞን አርአያ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ*

"ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ የመምህርነት ሙያና የትምህርት ጥራት ላይ በተጠናከረ ጥናት የተመሠረተ የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው፡፡"

*ዶ/ር መስፍን ሞላ ደምሴ፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ*

"... ይኸን መጽሐፍ በማንበባችሁ የመምህርነት ሙያ በኢትዮጵያ ከየት ወደ የት ለሚለው ጥያቄያችሁ ትክክለኛ ምላሽ ልታገኙ እንደምትችሉ ከፍተኛ ግምት አለኝ።"

*ፕሮፌሰር ሰሎሞን መለሰ፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ*

"ይህ መጽሐፍ ከአፀደ ህፃናት እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ላለው ተማሪና መምህር ምርጥና ድንቅ ትምህርት ቤት ሆኖ አግኝቻለሁ። ... ለመምህርነት ሙያ ክብር፣ ለመምህራን ብቃትና ክህሎት፣ እና ለትምህርት ጥራትና ለአገር እድገት ችግሮች ዝርዝር የመፍትሔ ምክረ-ሃሳቦችን አቅርቧል። ሁሉም ያድምጥ!"

*ፕሮፌሰር ተሰማ ኤርሱም፣ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ*

"ባጭሩም፣ ይህ የፕሮፌሰር አክሊሉ መጽሐፍ ሰሚ ሳይሆን አድማጭ ጆሮዎችን አግኝቶ ወደተግባር ከተመነዘረ፣ ለእኔ፡- ስም፣ ታይትል፣ ሞያ፣ ልምድ እና አገራዊ ስሜት ህብር "Harmony" ፈጥረው የተጣመቁበት ተምሳሌታዊ የትምህርት ጥም ማርኪያና የአገራዊ እድገት ፍኖት ተላሚ ሥራ እንደሆነ አምናለሁ፡፡"

*ዶ/ር ዳዊት አዲሱ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ*

"ይህንን መጽሐፍ ካነበባችሁ በኋላ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ህብረተሰቡ፣ የትምህርት ቤት ኃላፊዎችና መንግሥት ትኩረት በመስጠት የመምህራንን ህይወትና በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ላይ የአቅማችሁን አስተዋፅኦ ታደርጋላችሁ ተብሎ ይጠበቃል።"

*ፕሮፌሰር ሙሉጌታ አጥናፉ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ*

"አገራችንን እየመሩ ያሉ ትላልቅ ባለስልጣናት እና ምሁራን ጭምር ይህን መጽሐፍ አንብበው ከገጠመን የትምህርት ቀውስ እንድንወጣ የድርሻችንን ለመወጣት የዕቅድ መነሻ ይሆናል ብየ አምናለሁ፡፡"

*ሽመልስ አበበ፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) ም/ፕሬዚዳንት*

"... ትኩረት ለተነፈገው ሙያ ትኩረትን፣ ለአንባቢያን በስነትምህርት ሳይንስ ጠብሰቅ ያለ እውቀትን፤ በዘርፉ ላሉ ምሁራን ከተምሳሌትነት በተጨማሪ የማጣቀሻ ጽሁፍ አግልግሎትንና ለማህበረሰቡና ለመንግስት ደግሞ አገርን ለመታደግ የማንቂያ ደወል የመሆን አገልግሎት እንዲሰጥ ስለመዘጋጀቱ ረቂቁን ሳነብ በደንብ ተረድቻለሁ፡፡"

ፕሮፌሰር በላይ ተፈራ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

"የትምህርት ባለሙያዎች፣ በታሪክ አጋጣሚ ያለበቂ ልምድና የትምህርት ዝግጅት በየደረጃው የትምህርት ስርዓቱን እየመሩ ያሉ፣ እንዲሁም የተማሪ ወላጆች ይሄንን መጽሐፍ ቢያነቡ እንደሚጠቀሙ ላስገነዝብ እወዳለሁ። በትምህርት ስርዓቱ ስለሚታየው ውድቀትና ውዥንብር መንፈሳዊ ህመም የሚሰማቸው ሁሉ መጽሐፉን እንዲያነቡ እመክራለሁ።"

ፕሮፌሰር አምብሳ ቀነአ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

"በትምህርትና በአጠቃላይ ሀገራዊ ልማት ላይ አትኩረው የሚመራመሩ ምሁራን፤ በቅደመ-ምረቃና በድህረ-ምረቃ ደረጃ ላሉ ተመራማሪዎች እንዲሁም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ እጅግ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው፡፡"

ፕሮፌሰር ተስፋዬ ሰመላ፣ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

"... ከፍተኛ ልብ አንጠልጣይ ግርምትን የሚጭሩ፤ የሚያስደንቁ በአንፃሩ ደግሞ እጅግ የሚያሳዝኑ፤ የሚያስደምሙ የመምህርነትና መምህራን አገርአቀፍና ዓለምአቀፍ ጉዳዮችን የሚዳስስ ነው፡፡ ምናልባትም እኔ በሙያው ውስጥ ስላለሁ ነው መሰለኝ በታሪኩ በጣም ልቤ ተነክቷል፡፡"

ዶ/ር ሐረገወይን ፋንታሁን፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ



አክሊሉ ዳለሎ (ፕሮፌሰር)

ፕሮፌሰር አክሊሉ ዳለሎ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጂኦግራፊና አካባቢ ትምህርት ፕሮፌሰር ሲሆን በዚሁ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪውን በጂኦግራፊና ሁለተኛ ዲግሪውን በካሪኩለምና ኢንስትራክሽን አግኝቷል። ቀጥሎም ጀርመን አገር ከሚገኘው የዩሮፕያን ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ፍለንስቡርግ የማስተር ኦፍ ሳይንስ ዲግሪ በተለዋጭ ኢነርጂ ሲስተምና አስተዳደር እና የፒኤችዲ ዲግሪ በጂኦግራፊና አካባቢ ትምህርት አግኝቷል። ከ1981 ዓ/ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማስተማርና በተለያዩ የምርምር ሥራዎች እየተሳተፈ የሚገኝ ሲሆን ዘርፈ-ብዙ ሙያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችንም አበርክቷል። ከእነዚህ መካከል በቅርቡ ተጠናቅቆ ሥራ ላይ የዋለውን የኢትዮጵያ ትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ካስተባበሩ ስድስት የአገራችን ምሁራን አንዱ በመሆንና የመምህራን ትምህርት ዘርፉን ደግሞ በመምራት ያገለገለበት ተጠቃሽ ነው።

ፕሮፌሰር አክሊሉ በሰለጠነባቸው የሙያ ዘርፎች በርካታ ምርምሮችን ያደረገና እያደረገ የሚገኝ ሲሆን ውጤቶቹም በአገራችንና ከአገር ውጭ በሚታተሙ እውቅ መጽሔቶች ለንባብ በቅተዋል። በአሁኑ ወቅት ዋነኛው የምርምር ትኩረቱ በ"ሙያና ባለሙያነት" ላይ ሲሆን ይህ መጽሐፍ የዚህ ምርምር የመጀመሪያው ትሩፋት ተደርጎ ሊታይ ይችላል።

ISBN 978-99990-0-803-7

750.00 ብር
25.00 USD

20% ቅናሽ ለኢትዮጵያ መምህራን

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት